Amhariska

# ሁላችንም ዳግም ግልጋሎትን በተገበርን ግዜ አሸናፊ እንሆናለን

FÖRPACKNINGS & TIDNINGS INSAMLINGEN




ሁልግዜም ማሸጊን ወይም ጋዜጣን በዳግም መገልገያ ውስጥ በጣልን ግዜ፣ *ይህ የትልቅ ነገር መጀመሪያ ነው፡፡*

አሮጌ ጠርሙስ ለአዲስ የመኪና አካል መስሪያነት ሊውል ይችላል፡፡ ለምሳሌ የዱቄት ሳሙና ማሸጊያ ለአዲስ የጫማ ሳጥን መስሪያ ይሆናል፡፡ የትላንትናው ጋዜጣ የነገው ዋና ርእስ ሊሆን ይችላል፡፡ የተፈጥሮ ጥሬ አካላት እንደገና ለግልጋሎት የሚውሉና ከፍተኛ መጠን ያለው ሀይልም ይቆጠባል፡፡ እንዲህ በማድረግም እኛ የምንኖርበትን የተሻለ ዓለም ለመፍጠር ሁላችንም እገዛ እናደርጋለን፡፡

## ዳግም አገልግሎት

ሁሉም ማሸጊያዎችና ጋዜጦች ሰብስቦ ወደ ዳጋም አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በመውሰድ ወደ አዲስ ማሸጊያ ወይም ምርቶች መቀየር ይቻላል፡፡ የጠርሙስና ወረቀት ማሸጊያ ብዙ ግዜ ለበለጠ ማሸጊያነት ይውላል፡፡ የብረት ማሸጊያ ለፌሮዎች መስሪያነት ሲያገለግል አሮጌ ጋዜጣ ደህሞ ለማብሰያ ቤት ወረቀት ወይም ለጋዜጣ ህትመት በድጋሚ መዋል ይችላል፡፡

## የአምራች ሀላፊነት

በሲውድን የአምራች ሀላፊነት የሚባል ደንብ አለን፡፡ ማሸጊያን የሚያመርቱ ወይም የሚሸጡ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን የመሰብሰብ ወይም እንደገና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው፡፡በ Förpacknings- och Tidningsinsamlingen፣ FTI፣ በእነዚህ ድርጅቶች ፋንታ እንሰራለን፡፡ ይህንን ለማሳካት የእርሶን እገዛ እንሻለን፡፡

## የዳግም አገልግሎት ጣቢያዎች

ኤፍቴአይ (FTI) የዳግም አገልግሎት ጣቢያዎችን በመላ በሲውድን የተከለ ነው፡፡ ጋዜጣዎችን፣ የፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ብረትና ጠርሙስ ማሸጊያዎችን ወደ ዳግም አገልግሎት መስጫው መከተት ይኖርቦታል፡፡ ማእከላዊ የዳግም አገልግሎት መስጫ ማእከል ባለው አፓርታማ ላይ የሚኖሩ ከሆነ፣ ማሸጊያዎትንና ጋዜጦችዎን ወደዛ ይውሰዱ፡፡

## ተጨማሪ መረጃ

በ www.ftiab.se/ በቅርብ ያለን የዳግም አገልግሎት ጣቢያን ለማግኘትና መቼ ባዶ እንደሚሆኑና እንደሚጸዱ ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ የማሰናጃ መመሪያ፣ የዳግም አገልግሎት ቪዲዮዎች፣ መላዎችና ምክሮች፣ በተጨማሪም እዚህ ስላለው ድርጅት መረጃን ለማግኘት ይችላሉ http://www.ftiab.se/hitta-atervinningsstation

ስለ ዳግም አገልግሎት ላይ ስሚውሉ ጋዜጦችና ማሸጊያዎች ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካሎት፣ እባክዎን በ kontakt@ftiab.se ያግኙን ወይም በ 0200 88 03 11 ላይ ይደውሉ፡፡ ብዛት ባላቸው ውጋጆች፣ ድርጅቶች፣ የኤሌክትሪክ ውጋጅ ወይም ሌሎች የማስወገጃ ጉዳዮች ላይ ለሚኖር ጥያቄ፣ እባክዎን በአካባቢዎ ያሉ ባለስልጣናትን ያግኙ ወይም በ www.sopor.nu ላይ የበለጠ ያንብቡ፡፡

# የበለጠ ማሰናዳት

የበለጠለ ቁሻሻን እንደገና አገልግሎት ላይ ለማዋል የእርሶን እገዛ እንሻለን፡፡ ሁሉም ማሸጊያዎች ሙሉ ለሙሉ ባዶና በተወሰ መልኩም ደረቅ መሆን አለባቸው፡፡ ከአንድ በላይ ቁስ የተሰሩ ማሸጊያዎች ካሉት፣ የበለጠ ክብደት አለው ብለው በሚያስቡት ቦታ ላይ ያድርጉ፡፡
እናመሰግናለን፡፡



## የፕላስቲክ ማሸጊያዎች

ለምሳሌ፣ ጠርሙሶች፣ ቆርቆሮዎች፣ የፕላስቲክ መያዣዎች፣ የሚሞሉ ማሸጊያዎች፣ የፕላስቲክ ቱቦዎችና ስታይሮፎም፡፡

- ቆርኪዎችንና ክዳኖችንም ማስወገድ ያስፈልጋል። የፕላስቲክ ማሸጊያዎች የተሰበሰበበት መዣውን ለየብቻው ወደ ማከማቻው ገንዳ መጣል። ይኸም ዳግም የማምረቱን ሥራ ያቀላጥፋል።
- ለምሳሌ እንደ የቤት እቃና አሻንጉሊት ያሉ ማሸጊያ ያልሆኑ የፕላስቲክ ምርቶች ትላልቅ እቃዎች በሚመለሱበት ማእከላዊ ጣቢያ ወይም ከቤት ውስጥ ትራፊዎች ጋር ሊለዩ ይችላሉ፡፡ በመያዣ የተገዙ የፕላስቲክ ጠርሙሶችንም በሱቆች ውስጥ በመመለስ የተያዘውን ገንዘብ ማስመለስ ይቻላል።



## የወረቀት ማሸጊያዎች

ምሳሌ፤ የፓስታ ማሸጊያ፣ የወተትና ጭማቂ ካርቶኖች፣ የጫማ ሳጥኖች፣ የሽንት ቤት ወረቀት ካርቶኖችና የካርቶን ሳጥኖች፡፡

- ጠፍጣፋ ማድረግና ለሁለት ማጠፍ። ቦታ ለመቆጠብ ትንንሾቹን ማሸጊያዎች በትልልቆቹ ውስጥ ማስገባትም ተገቢ ነው።
- ፖስታዎች የሚመለሱት ከመደበኛው የምግብ ትራፊ ወይም የሚቃጠሉ ቆሻሻዎች ጋር ነው። ጋዜጦች፣ የማስታወቂያ በራሪ ወረቀቶችና የመሳሰሉት የሚመለሱት ደግሞ በጋዜጣ ማከማቻ ገንዳ ውስጥ ነው።



## ብረት ነክ ማሸጊያዎች

ምሳሌ፤ የቆርቆሮ ጣሳዎች፣ ባዶ የመርጫ ቆርቆሮዎች፣ ቱቦዎች፣ ቆርኪዎች፣ ክዳኖች፣ ባዶ የቀለም ቆርቆሮዎች።

- በጣሳዎቹ ውስጥ ያለውን ሹል ወይም ስል ጫፍ ማጠፍ ያስፈልጋል።በቱቦዎቹ ላይ ያለውን ክዳን ግን እዚያው ላይ መተው ይቻላል።
- ባለቀለም እና የሙጫ ትራፊ ያላቸው ጣሳዎች መወገድ ያለባቸው በጎጂ ነገሮች ምድብ ነው። ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች፣ የቧንቧ ክፍሎች፣ የምግብ መጥበሻዎች፣ ሌሎችም ማሸጊያ ያልሆኑ ነገሮች ትላልቅ እቃዎች በሚመለሱበት ማእከላዊ ጣቢያ ወይም ከቤት ውስጥ ትራፊዎች ጋር ሊለዩ ይችላሉ። የመጠጥ ጣሳዎች የተያዘ ገንዘብ በሚመለስበት ሱቅ ሊመለሱ ይችላሉ።



## የጠርሙስ ማሸጊያዎች

ለምሳሌ፤ ባለቀለም ወይም ቀለም አልባ ጠርሙሶችና ብልቃጦች፡፡

- ቆርኪዎች፣ ክዳኖችና ቡሾች በተገቢው ቁስ አይነት መለየት አለባቸው፡፡ ባለቀለምና ቀለም አልባ የጠርሙስ ማሸጊያዎችን በተገበቢው መያዣ መለየት፡፡
- በመያዣ የተገዙ ጠርሙሶች የተያዘ ገንዘብ በሚመለስበት ሱቅ ሊመለሱ ይችላሉ። የሸክላ እቃ፣ ሴራሚክና ሌሎችም ማሸጊያ ያልሆኑ ነገሮች ትላልቅ እቃዎች በሚመለሱበት ማእከላዊ ጣቢያ ወይም ከቤት ውስጥ ትራፊዎች ጋር ሊለዩ ይችላሉ። አምፑሎችና ፍሎረሰንቶች መወሰድ ያለባቸው በአካባቢው ባለ ባለስልጣን የዳግም አገልሎት ማእከሎች ነው።



## ጋዜጦች

ለምሳሌ፤ እለታዊና ሳምንታዊ ጋዜጣዎች፣ መጽሄቶች፣ ካታሎጎች፣ የማስታወቂያ በራሪ ወረቀቶች፣ ማስታወሻዎችና የመጻፊያ/የመሳያ ወረቀቶች

- የፕላስቲክ መጠቅለያንና ተለጣፊ ማስታወቂያ ማስወገድ፡፡
- ፖስታዎችና የተጠረዙ መጻህፍት በቤት ውስጥ ቆሻሻ ወይም ተቀጣጣይ ቆሻሻ መለየት አለባቸው፡፡ የወረቀት ቦርሳዎች፣ ካርቶኖችና ተመሳሳይ ነገሮች ለወረቀት ማሸጊያነት ተብለው በተሰሩ መጣያዎች ውስጥ መከተት አለባቸው፡፡

fti